# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ህዳር 21 ቀን 2007 ዓ.ም.

## ህዳር 22 አለም አቀፍ የኤድስ ቀን

ከ 1988 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ ዝግጅቶች፡ መግለጫዎችና ትዕይንቶች እየታጀበ በመላው አለም በያመቱ ህዳር 22 የሚታሰበው አለም አቀፍ የኤድስ ቀን ዘንድሮም ካለፈው በበለጠ ሁኔታ እንቅስቃሴ እየተደረገበት ይገኛል። መንግሥታዊ ተቋሞችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች በበሽታው የተጠቁ ዜጎች የሚደርስባቸውን አድሎና የመገለል ሁኔታ ለመግታት እንዲቻል ሁሉም ዜጋ ድምጹን እንዲያሰማና አንድነቱንም በተግባር እንዲገልጥ አፅንዖት የተሞላበት ጥሪ በማቅረብ እየዘከሩት እንደሚገኙ በተለያዩ የዜና ተቋማትና ድረገፆች የሚወጡት ዘገባዎች፡ ትንተናዎችና ትምህርታዊ ገለፃዎች የሚያመላክቱት ናቸው።

ይህ ቀሳፊ የሆነ በሽታ አስከፊነቱ በተለይ የጤና ተቋማትና የመድኃኒት አቅርቦት በተስፋፋባቸው ሀገሮች እየቀነሰ ቢመጣም በቫይረሱ እየተለከፉ ያሉት ግን ቁጥራቸው አሁንም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሆነ እየተገለፀ ሲሆን ድህነት ክፉኛ በሚያጠቃቸውና የብዙሃኑን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ታፍኖ በአናሳ ቡድኖች በተገነቡ አምባገነን ሥርአት የሚሰቃዩ አገሮች፡ መድሃኒት የመግዛት አቅማቸው ዝቅተኛ ወይንም ጨርሶ የሌለ በመሆኑ በሽታው እየተስፋፋ ከመሄድ አልተገታም። በጋምቤላ ለምሳሌ በበሽታው የተለከፉት ቁጥር ከ 6 በመቶ እንደሚበልጥ ይገመታል። ይህ አሃዝ ሲያዩት ቀላል ቢመስልም ከማህበራዊ ኑሮ አንፃር ሲታይ በተለይ በኤኮኖሚው መስክ ከፍተኛ ተሳትፎ አድራጊው የሆነው የሕብረተሰብ ክፍል ከግምት ሲገባ የመስፋፋት አቅሙ ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚያስከትለው አደጋ ምን ያህል አስጊ እንደሆነ የሚያመለክት መሆኑ ተደጋግሞም የተገለፀ ነው።

ባጠቃላይ በአለም አቀፍ ደረጃ በሽታውን ለመታደግ በመልካምነት የሚታዩ የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ከሥረ መሰረቱ ለማጥፋት ግን ገና ረዥም ርቅት መጓዝ እንደሚያስፈልግ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ይህ ሁናቴ በተለይም በወጣቱ መካከል መዘናጋት እያስከተለ የመጣ በመሆኑ ይህ እንዲታረም የተለያዩ ትምህርታዊ መልዕክቶችን በሕዝቡ መካከል በስፋት ማዳረሱ ወሳኝነቱ ጎልቶ እየታየ ነው። በመሆኑም በበሽታው ላለመለከፍ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ በተለይ በዚህ አመቱ አከባበር አፅንዖት በተሞላበት መልክ እየተገለፀ ይገኛል።





EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 30022
92276 Bois Colombes cedex
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

ይህ አለም አቀፍ የኤድስ ቀን በመላው አለም በሚከበርበት ወቅት በሀገራችን ከሥልጣን የተቆናጠጠው የወያኔ አገዛዝም በበኩሉ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የተወሰኑ በአገዛዙ ሰነድ ያካተታቸውን አንቀፆች እንደገደል ማሚቶ በማስተጋባት ይህንና ያንን አድርጌያለው እያለ ቢለፍፍም በተጨባጭ በመድረኩ የሚታየው ግን የተለየ እንደሆነ እንገነዘባለን። እየተሰጡ ያሉ መረጃዎችን በጥልቀት ለሚመለከት ሁሉ አሁንም በበሽታው የሚለከፉትና የሚሰቃዩት በርካታዎች መሆናቸውን ለመገንዘብ አያዳግትም። ከባዕዳን መንግሥታት የሚሰጡ የቁሳቁስና የንዋይ እርዳታዎች በአገዛዙ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ውሳኔ ለተረጂው በአግባቡ አይደርሱም። እንዲያውም በተለያዩ ወቅቶች መዘረፋቸው በወቅቱ የተገለፀ ቢሆንም ሳይታረም ቀጣይ ሆነዋል። የበሽታውን መስፋፋት በተወሰነ ደረጃ ለመግታት የሚቻልበትን ሁናቴ የወያኔ አገዛዝ በተለይም ክፉኛ በሚጠላቸው አካባቢዎች ይህ ነው የሚባል እርምጃ አለመወሰዱም የተገለፀ ነው። ይህ ሁናቴ የተወሰኑ የባዕዳን እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ጥረት ባይኖር ኖሮ ምን ያህል የከፋ ሊሆን እንደሚችል ማሰቡ በራሱ የሚሰቀጥጥ ነው።

የጤና ተቋማትን ብንመለከትም አገዛዙ እንደሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን መሆን የሚገባውን እንዳልሆነ የሚወጡ ጥናታዊ ዘገባዎች ያረጋግጣሉ። በኢትዮጵያ አሁንም በጣም ዝቅተኛ የሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ያሉባት ሀገር ናት። በ 2010 ዓ.ም. ለ 25 000 ዜጋ አንድ ዶክተር ነው ያለው። ይህ ሁናቴ ከአፍሪካ ለ 5000 ሰው  አንድ ዶክቶር መኖሩ ጋር ሲነፃፀር በጣም የሚያሳፍር ነው። በአንድ ጥናት እንደተጠቆመው በ 20 አመት ውስጥ ማለትም ከ 1987 እስከ 2006 ዓ.ም. 73.2 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን የሕክምና ዶክቶሮች ባብዛኛው ሊያገኙ ለሚችሉት አጓጊ ለሆነ ከፍተኛ ደሞዝ ወደ ውጭ ሀገር መጓዛቸው፡ እንዲሁም መንግሥታዊ ላልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ወይንም ደግሞ ወደግል ድርጅቶች መሄዳቸው ተገልጿል። በሀገሪቱ አሉ ከሚባሉት ሶስት ከፍተኛ የሕክምና ተቋማት ከተመሰረቱ ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ የተመረቁት 3728 ሲሆኑ ከዚሁ ጋር ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲገቡ እድሉን ለማግኘት የቻሉት  ግን በያመቱ 350 ብቻ ነበር። በዚህ መልክ ይህንን ቀሳፊ የሆነ በሽታ ካሉት የመድሃኒት አቅርቦት በሁሉም አካባቢ የማዳረሱ ችግር እንዳለ ሆኖ አግባብነት ባለው መልክ ለመታደግ ከፍተኛ ችግር ያለ እንደሆነ አመልካች ነው። ለዚሁ ሁሉ ጉድለት ተጠያቂው መልካም አስተዳደር እንዳይመሰረት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አፍኖ ነጠኛ የሆነ አምባገነን ስርአት የመሰረተው ተወጋዡ የወያኔ አገዛዝ እንጅ ሌላ አይደለም።

በመሆኑም ዛሬ ይህንን አለም አቀፍ የኤድስ ቀንን ስንዘክር ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ዜጎች በበጎ ፈቃደኝነትና  ባላቸው አቅም በሚገኙበት ቦታ ሁሉ በሽታውን አስመልክቶ ትምህርታዊ ገለፃ በማስፋፋት ለአብዛኛው ሕዝብ እንዲዳረስና ካለፈው በበለጠ ሕዝባዊ መነቃቃት እንዲፈጠር ማድረግ የሚጠበቅና ወሳኝነት ያለው መሆኑ በጥብቅ ሊገነዘቡት የሚገባ ነው። ይህም በበኩሉ በበሽታው የተለከፉትን በሚመለከት የምክርና



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

የህክምና አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበት ሁናቴ ማመቻቸትንም የሚያጠቃልል ይሆናል። ማንኛውም ግለሰብ ዜጋ በተለይም በኤኮኖሚው መስክ ወሳኝ ተሳትፎ የሚያደርጉ የሕብረተሰብ ክፍል አባላት ኃላፊነታቸውን እንዲገነዘቡና በበሽታው ላለመለከፍ መውሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በአለም አቀፍ ደረጃ የቀረበውን ጥሪ ኢሕአፓ በመደገፍ ይተባበራል። ለስኬታማነቱም የበኩሉንም ጥረት ያበረክታል።

የተጠቁ ዜጎችን መንከባከብ የሁሉም ኃላፊነት ነው!



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**